# ጉደኛው አቶ አብርሃም ያዬህ ብቅ አሉ!

አምዴ ደጀኔ

ሰውየውን አንቱ ያልኳቸው በሀገር ልምድ የተነሳና በዕድሜም በጣም ስለሚበልጡኝ እንጂ እንጨትም ይሸብታል የሚያሰኙ መሆኑን አውቃለሁ ። አቶ አብርሃም ከብዙ ዓመታት ከመድረክ ወመገድ በኋላ ያለፈ ታሪካቸውንና ድርጊታቸውን መርምረው ተሻሽለው ይገኛሉ ያለ ከነበር ማፈር መታዘብ ተገዷል ። የተያያዘው ጥያቄ ግን ይህ የቀድሞ የደርግ ወታደርና የአውስትራሊያ ራዲዮ አማርኛ ክፍል ሀላፊ ግለሰብ ሁሌም አጠያያቂ ግለሰቦችን ለምንስ ከጉድጓድ እያወጣ መድረክ እንደሚሰጥ ነው ።ይህን ብልም አቶ አብርሃምን ከወታደር ካሳሁን እንግዳ ከመንግስቱ፤ፍቅረ ሥላሴና ፍስሃ ደስታ ወዘተ በማወዳደር አይደለም ።

አቶ አብርሃም ያየህ ከወያኔ ኮብልለው ወደ ደርግ ከመግባታቸው በፊት በደርግ ግዜ በሰላም በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ ናቸው ። ለምን እንደኮበለሉ አላውቅም። የሠራተኛ ማህበራት መሪ ነበርኩ ያሉት ግን ሃሰት መሆኑን ብዙዎች ይናገራሉ ። ደርግን ተቃዋሚ የነበሩ የሠራተኛ ማህበር መሪዎች እነ ማርቆስ ሐጎስና ግርማቸው የእሳቸው የስራ ጓደኛ ሳይሆኑ ተደብቀው የታገሉ የሠራተኛ መሪዎችና ኢህአፓ ተብለውም የተገደሉ ናቸው ። በዚያን ወቅት አቶ አብርሃም ወይም ወደ ስደት ወጥተዋል አለበለዚያም ከደርግ ጋር ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩ የቢሮ ሠራተኛ ነበሩ ። ታጋይ ነበርኩ፤መሪ ነበርኩ ማለት የአቶ አብርሃም የተለመደ ውሸት መሆኑን በሚገባ የሚያውቋቸው ይናገራሉ ።ወደ ሱዳን ተሰደው ሳለ አቶ አብርሃም ለወያኔ በኦዲትነት-ነጋዴነትና በደህንነት ሰርተው መዋጮ ያልከፈሉ ስደተኞችን እያጋለጡም ጉዳት አድርሰዋል ተብለው ሲወነጀሉ አድምጠናል ። ከወያኔ በምን እንደተጣሉ ባይታወቅም ወደ ደርግ ሲኮበልሉ በራዲዮና  ቴሌቪዥን ታላቁ ሴራ ብለው ወያኔን ማጋለጣቸውን ባላይም በጽሁፍ አንብቤ ምስክር ነኝ ። ሌሎች ግን ደርግን ሊያወናብዱ የተላኩ ናቸው እንደሚሉም ሰምቻለሁ ።ይሁን አይሁን ባላውቅም አቶ አብርሃም ወያኔ ለስልጣን ሲደርስ ከአዲስ አበባ ሸሽተው ወደ ኬንያ መግባታቸውን ባለሁበት ከተማ ሰምቼ ከተደሰቱት አንዱ እንደነበርኩ መደበቅ አልፈልግም ።በአዲሱ ስደታቸውም ጸረ ወያኔ ሆነው ቀጥለዋል ሲባል መስማት ብቻ ሳይሆን ሴቶችን ደበደቡ ዘረፉ በሚል በዩጋንዳ ሲታሰሩ ዛሬ ወያኔ ጋ አዘዞ ያሉት ነርስ እማዋይሽ እርዳታ ሲሰበስቡ የአቅሜንም አድርጊያለሁ ። አቶ አብርሃምም ወደ ዋሺንግተን ተጋብዘው ሲመጡና ሲናገሩ ከታዳሚያቸው አንዱ ነበርኩ። እሳቸውም ገቢውን ሰው ሲቆጥሩ ቆይተው በኋላ ከገንዘቡ ድርሻዬ ይሰጠኝ ብለው ከጋብዟቸው ከተከበሩ ልዑል ኤርምያስና ዶክተር አክሊሉ ጋር ጭቅጭቅ ገቡ ሲባልም ራሴን ደፍቼ ምነዋ ማለትን መጀመር ተገድጃለሁ ። አቶ አብርሃም የሚያውቋቸው እንደሚሉት ገንዘብ ወዳድ፤ተራ ለፍላፊና ዋሾ ናቸው ለሚለው ድምዳሜዬ የመጀመሪያ የጥርጣሬ ድንጋይ ሆኖልኛል ማለትም እችላለሁ ።ያኔ ግን ብዙ አድናቂዎችና ተከላካዮች ስለነበሯቸው የተዘረፉትና የተደበደቡት ሴቶች ማንም አማኝን አላገኙም ።

ይህን ሁሉ መዘርዘር የፈለግኩት በሂደት እንዴት የኚህን ሰውዬ ቀላልነትና ዋሾነት ፤ኋላም የትግሬ ትምክህተኛነት ማወቅ እንደቻልኩ ለማቅረብ ነው ። አት አብርሃም ከእስር ተፈተው ወድ አውሮጳ ሲሰደዱ ወደ አሜሪካም ሆነ እዚያው በአውሮጳ ዲያስፖራው ከጎናቸው ቆሞ እርዳታ ለግሷቸዋል ። የወያኔ ጠናካራ ተቃውሚ ናቸው በሚልም በየሀገሩ ተጋባዥ ሆነው ቅስቀሳውም ተደምጧል ። ከእሳቸው ባልተናነሰ ወያኔን ያጋለጠው ገብረ መድህን አራያን ይህን ያህል ያቋጠረው እንዳልነበረ መጠቀስ ያለበት ነው ።ገብረ መድህን አርአያ ግን ሀቁን እየተናገሩና ጸረ ወያኔ ሆነው እስካሁንም

ጸንተው እንዳሉም የማያውቅ የለም ። አቶ አብርሃም ያየህ ታዲያ በሚያሳዝን ሁኔታ ቀስ በቀስ ጭምብላቸውን አውልቀው ጸረ አማራ አቅዋማቸውን ግልጥልጥ አድርገው ሊያሳዩን ጀመሩ ። ቦታውን አሁን ብዘነጋውም በአንድ የአውሮጳ ከተማ ስብሰባ ላይ በአማራው ላይ የጭቃ ጅራፋቸውን አጮሁና ጭቁንና ተበዳይ ያሉትን ኦሮሞ ሕዝብ ቢገነጠል ሲገባው ነው ወዘተ በሚል የወያኔን ከፋፋይ ፕሮፓጋንዳ አስተጋቡ ። የደገፋቸው ሁሉ ምነዋ ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ ብሎ ተገረመ ። ለምንስ የኦሮሞን ሕዝብ ብሶት የተባለውን አስተጋቡ በማለት ሳይሆን ግንጠላን በመደገፋቸውና እንደ ዛሬው የአኖሌ ሀውልት ዓይነት ቅጥፈትና ጸረ አማራነት በማሰማታቸው ነበር ታዳሚው ሁሉ የተገረመው ። አቶ አብርሃም ሽፋፍነው የነበረውን ወያኔነትና ጸረ አማራነት በ1997ኡ ምርጫ ጊዜ እንደማንኛውም ትምክህተኛ ግልጽ አድርገው (ሁሉም በወያኔ ሸንፈት ደንግጥው ነበርና) ወጥተዋል ። ጠላታችን ያሉትንም መለስ ልክ እንደ አዜብ ሲያዳንቁም--በከተማችን ባለው የወያኔ ሰላም ራዲዮ ሳይቀር-ተደምጠዋል ። ጸረ ሻዕቢያ ነኝ ሲሉ የከረሙትና ሲለፍፉ የነበሩት አቶ አብርሃምም አለምንም ስጋት ሰተት ብለው አስመራ ገብተው የዴምኅት የውጭ ጉዳይ ሀላፊ ሆኜ ተመለስኩ ሲሉም በተጨማሪ ዲያስፖራው አክ እንትፍ ብሎ ከትቢያ ጥሏቸዋል ። አቶ አብርሃምን ጋባዥ ጠፋ--ፓልቶክ የለ፤ቃለ መጠይቅ የለ ። ወደ ቆሻሻ ሰብሳቢው sbs ቃለ መጠይቅ የመጡትም ራሳቸው ለምነው ሳይሆን አይቀርም ባይ ነኝ:: በደርግነት ስለሚገናኙ ፤ሁለቱም ለተስፋዬ ወልደ ሥላሴ ሰርተው ሕይወት አስጠፍተዋልና።

ታዲያ አሁን ከስንት ዓመት የተገለለ የከሰረ ኑሮ በኋላ አቶ አብርሃም ያዬ ለምን ብቅ አሉ? አሁን ምን ወያኔ አድን ሚና ያዙ?ተሰጣቸው? ይህን ሁላችንም እንመርምረው ። አቶ አብርሃም ግን ከወደቁበት ትቢያ መነሳት ያለባቸው ሰው አይደሉም ። በፖለቲካ ሲነግዱ የነበሩት በቃ ተብሏልና በዚያው በተወገዱብት በተጣሉበት ቢከርሙ የተሻለ ይሆናል ። ውሎ አድሮ ለትግሬነታችው ቅድሚያ ሰጥተው በአማራ ላይ፤ በኢትዮጵያ ላይ የሚነሱ ያው ወያኔወይም ወያኔ አድን ትግሬ መሆናቸው ታውቋል ። ተገላግለናቸውና እፎይ ተመስገን አምላኬ ብለን ነበርና ተመልሰው አይነጅሱን ። አቦ የሰለቹን ሰው ናቸው።

ለትምክህተኞችና ጸረ አማራዎች ጆሮና መድረክ አንስጥ !
ድል ለስፊው የኢትዮጵያ ህዝብ